የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፳
አዲስ አበባ ሚያዚያ ፲፱ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

29th Year No. 20
ADDIS ABABA, 27th April, 2023

**<u>ማውጫ</u>**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፹፭/፪ሺ፲፭

ለሁለተኛው ምዕራፍ የዘላቂ መሬት አያያዝ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ……………………….ገጽ ፲፬ሺ፯፻፴፱

**<u>Content</u>**

Proclamation No. 1285/2023

International Development Association Loan Agreement for Financing Second Ethiopia Resilient Landscapes and Livelihoods Project Ratification Proclamation…....Page 14739

**አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፹፭/፪ሺ፲፭**

**<u>በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ</u>**

ለሁለተኛው ምዕራፍ የዘላቂ መሬት አያያዝ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል የ፩፻፯ ሚሊዮን ፩፻፸፬ ሺ ፪፻፶፭ (አንድ መቶ ሰባት ሚሊዮን አንድ መቶ ሰባ አራት ሺ ሁለት መቶ ሃምሳ አምስት) የአሜሪካን ዶላር ብድር የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል ነሐሴ ፪ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህን ስምምነት የኢ.ፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መጋቢት ፳፩ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም በአካሄደው ፲፪ኛ መደበኛ ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

**PROCLAMATION NO. 1285/2023**

**<u>A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONL DEVELOPMENT ASSOCIATION</u>**

**WHEREAS,** the Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association shall provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan an amount of One Hundred Seven Million One Hundred Seventy-Four Thousand and Two Hundred Fifty-Five Dollars (US$107,174,255) for financing Second Ethiopia Resilient Landscapes and Livelihoods Project, was signed in Addis Ababa, on 8th Day of August, 2022;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said agreement at its 12th ordinary session held on 30th Day of March, 2023;

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "ለሁለተኛው ምዕራፍ የዘላቂ መሬት አያያዝ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፹፭/፪ሺ፲፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. <u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል ነሐሴ ፪ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር GCF Loan Number TF0B8450 በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

**፫. <u>የገንዘብ ሚኒስቴር ሥልጣን</u>**

የገንዘብ ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን የ፩፻፯ ሚሊዮን ፩፻፸፬ ሺ ፪፻፶፭ (አንድ መቶ ሰባት ሚሊዮን አንድ መቶ ሰባ አራት ሺ ሁለት መቶ ሃምሳ አምስት) የአሜሪካን ዶላር በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሚያዚያ ፲፱ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም**

**ሣህለ ወርቅ ዘውዴ**
**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ**
**ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**NOW, THERFORE,** in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Loan Agreement for Financing Second Ethiopia Resilient Landscapes and Livelihoods Project Ratification Proclamation No. 1285/2023".

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

The Loan Agreement Number GCF Loan Number TF0B8450 signed in Addis Ababa, on 8th Day of August, 2022, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association is hereby ratified.

**3. <u>Power of the Ministry of Finance</u>**

The Ministry of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan an amount equivalent to One Hundred Seven Million One Hundred Seventy-Four Thousand and Two Hundred Fifty-Five Dollars (US$107,174,255) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

**4. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force up on its publication in the Federal Negarit Gazettee.

**Done at Addis Ababa, On this 27th Day of April, 2023**

**SAHLE-WORK ZEWDIE**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL**
**DEMOCRATIC REPUBLIC**
**OF ETHIOPIA**